# የፋሲካው በግ

በግ ሥጋው ለመሥዋዕትና ለምግብ፣ ጠጉሩና ቆዳው ደግሞ ለልብስ የሚሆን የዋህ የቤት እንስሳ ሲሆን በራሱ የመከላከል ኃይል ሰለሌለው እረኛ አስፈልጎታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በጎችን ለመሥዋዕት ማቅረብ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ ተግባር ነበር፡፡ አቤል ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት በግ ነበር፡፡ አብርሃም በልጁ በይስሐቅ ፈንታ ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት እግዚአብሔር ያዘጋጀውን በግ ነው፡፡ በተለይ በእስራኤል በግ ለፋሲካ በዓል መሥዋዕት ሆኖ ይታረድ ነበር፡፡

ፋሲካ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ “ ፈሳሕ” ማለት ሲሆን አለፈ፣ ተሻገረ፣ አመለጠ የሚሉ ትርጉሞችን ያመለክታል፡፡ የእስራኤል ልጆች በግብጽ አገር አርደው ደሙን በደጃፋቸው በመርጨት ከእግዚአብሔር ቁጣ አምልጠው ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ በዚያች ሌሊት ግብጻውያንን ሲቀሥፍ፣ ደም በነበረበት ቤት አልፎ ስላልገደለ ወይም ደም የተረጨበትን ቤት ስላለፈ ያ ቀን ፋሲካ ተባለ፡፡ በዚህ የተነሳ ለፋሲካ በዓል የሚታረደው በግ የፋሲካ በግ ተብሎ መጠራት ጀመረ፡፡

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስራኤል በበጉ ደም ከሞት ያመለጡበትን ቀን በማስታወስ በየአመቱ የፋሲካን በዓል በግ እያረዱ ያከብሩ ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች ለእውነተኛው የእግዚአብሔር በግ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምልክት ነበር፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት የተሰቀለው የፋሲካ ሳምንት ነበር፡፡ ክርስቶስ ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ደሙን ስላፈሰሰልን “ፋሲካችን ክርስቶስ” ተባለ፡፡ (1ቆሮ. 5÷7፣ 1ጴጥ. 1÷08-09)

ስለሁላችን ኃጢአት እና በደል እንዲሁም መተላለፍ የቆሰለ፣ ስድባችንን የተሰደበ፣ ውርደታችንን የተዋረደ እና ሞታችንን የሞተ በደሙ ከኃጢአታችን ያነጻን እና ከሞት ያስመለጠን ክርስቶስ ስለሆነ የክርስቶስ ትንሣኤ በዓል ፋኪሳ ተብሎ ይጠራል፡፡ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ በበጉ ደም የተረጩ፣ የታጠቡና የታተሙ በመሆናቸው ትንሣኤ አላቸው፡፡ ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች እረኛቸውን ክርስቶስን የሚከተሉ በጎች በፍርድ ቀን በክርስቶስ ቀኝ የሚቆሙ ሆነው ተመስለዋል፡፡ በግ ንጹሕና የማይጎዳ የዋህ እንስሳ ስለሆነ ሐሰተኞች የዋህ ለመምሰል በግ መስለው እንደሚመጡ ጌታ ተናግሯል፡፡ (ማቴ. 7÷05)

ጥያቄዎች፡- 1. በመጽሐፍ ቅዱስ በግ የምን ምሳሌ እንደሆነ ዘርዝሩ?

2. ፋሲካ ማለት ምን ማለት ነው?

3. የፋሲካ በዓልን ማክር መቼ ነው የተጀመረው?

4. ክርስቶስ ፋሲካችን ነው የተባለው ለምንድነው?

5. የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ማን ነው?



# መጻጉዕ

በቤተ ሳይዳ አንድ በጣም የታመመ በመጠመቂያ ተጠምቆ ለመዳን ሲጠባበቅ ለ38 ዓመት በአልጋው ተኝቶ የቆየ ሰው ነበር።በሽታው ሰውነቱን በተልይም እጁና እግሩ ማዘዝ አይችልም (መሄድ አይችልም) ነበር። መጻጉዕ ማለት “በሽተኛ” ማለት ነው፡

ቤተ ሳይዳ (ቤተ ስዳ ማለት ‹‹ቤተ ሣህል (የጸጋ/የምህረት ቤት)) ቤተ ሳይዳ በገሊላ አውራጃ የምትገኝ ከተማ ነበረች፡፡ በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ስዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት። (ዮሐ 5፥2)›ቤተ ስዳ ባለ አምስት በር፥ መመላለሻ አንካሶች ፥ ሰውነታቸው የሰለለ ፥የውስጥ በሽታ ያለባቸው ፈውስን ከመጠመቂያው ውኃ ሲጠባበቁ የሚኖሩባት ቦታ ስትሆን የጌታችን ማዳን የተገለጠባት ሥፍራ ናት። የእግዚአብሔር መልአክ ውኃውን ሲባርክ (ሲያናውጥ) ቀድሞ ቶሎ የገባ የሚነጻባት (ከበሽታው ሁሉ የሚድንባት) ቦታ ናት ፡፡ በዕለቱ ከአንድ ሰው በቀር ለሌላው ፈውስ የማይደገምባት ቦታ ነበረች(መጀመሪያ ወኃው ውስጥ ቀድሞ የገባ ይድናል)። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እዚያ ሄደና ይህንን በአልጋ ለ38 ተኝቶ የነበረውን ሰው ጠየቀው ።

※ጌታችን መጻጉን ‹‹ልትድን ትወዳለህን››?

፨መጻጉዕ ግን ‹‹ሰው የለኝም›› ብሎ መለሰለት ይህንን ያለው ጌታችን ያድነኛል ብሎ ሳይሆን ‹‹ወደ መጠመቂያው ያደርሰኛል›› ወይም ‹‹አብረውት ካሉት አንዱን አዝዞ ወደ መጠመቂያው እንዲያደርሰኝ ያደርጋል›› ብሎ ነበር፡፡ይህ በሽተኛ ሰው ጌታችን ኢየሱስን አላወቀም ነበር፡፡

※ጌታችን መጻጉን ‹‹ተነስተህ አልጋህን ተሸከመህ ሂድ›› አለው። ባላሰበው ባልጠበቀው መንገድ ፈወሰው፡፡ ይህ ሰው ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ ሲጠባበቃት የነበረችውን የቤተ ሳይዳ ጠበል ሳያገኝ ፣ በመልአኩ መውረድ ሳይሆን በመላእክት ፈጣሪ ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈወሰ፡፡

፨መጻጉዕም ወዲያው ዳነና ቆመ፥ መሄድም ቻለ ፥ የሚካበደውንም የብረት አልጋ ተሸክሞ ሄደ።

※ኢየሱስም መጻጉዕን እንዲህ አለው ‹‹ከዚህ የባሰ እንዳያገኝህ ዳግመኛ አትበድል›› ብሎ ማስጠንቀቂያ ሰጠው ።

፡፡መጻጉዕ የተፈወሰበት ቀን በሰንበት ቀን ስለነበር አልጋውን ተሸክሞ ሲሄድ አይሁድም በሰንበት አልጋህን ልትሸከም አይገባህም ሲሉት „ያዳነኝ እሱ አልጋህን ተሸከመህ ሂድ አለኝ“ አላቸው።አይሁድም ሲጠይቁት መጻጉዕ ያዳነው ሰው ማን እንደሆነ አላወቀም ነበር ።ሲያሳያቸው አልቻለም ።ነገር ግን በሌላ ቀን በምኩራብ አግኝቶት ያዳነውን እንዳወቀውም ሄዶ ለአይሁድ ያዳነኝ እርሱ "ጌታ ኢየሱስ ነው" ብሎ ነገራቸው፡፡መጻጉዕ ግን ኢየሱስን ክርስቶስን ለመስቀል ፥ የሐሰት ክስ ሲቀርብበት ቀድሞ ወደ መጠመቂያው እንኳ ለመቅረብ አቅም ያልነበረው በሽተኛ ፤ ያዳነውን ረሳ፤ በሐሰትም መሰከረበት፤ በሙሉ ኃይሉ የአምላክን ጉንጮች በጥፊ መታ ።

1 ቤተ ሳይዳ የት ተገኛለች ?---------------------------------------------------------

2 መጻጉዕ ማለት ምን ማለት ነው ? ---------------------------------------------

3 በቤተ ሳይዳ በቅን ስንት ሰው ይድን ነበር ? ------------------------------

4 በሽተኞቹ የሚድኑት መቼ ነበር ? ------------------------------------

5 ጌታችን መጻጉዕን ሲያድነው ሲል ምን አለው? -----------------------------------

------

6 መጻጉዕ አልጋውን ተሸክሞ የሄደበት ቀን ምቼ ነበር ? ---------------------------

---------------

7 መጻጉዕ የጥሩ ሰው ምሳሌ ነው (አብራራው)

______________________________________

-----------------------------------------------------

------------------------------------------

# የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት

**አዳም አትብላ የተባለውን እጸ በለስ በልቶ ከገነት ሲባረር እግዚአብሔር ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ከ5500 ዓመት በኋላ አንድኃንለሁ ብሎ ቃል ገብቶለት ነበር ።በዚህም መሠረት አውግስጦስ ቄሳር የሮም ገዥ፣ ሄሮድስ የይሁዳ ንጉስ፣ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በቤተልሔም ተወለደ (በሥጋ ተገለጠ)፡፡**
**በዚያ ወራት ሰው ሁሉ እንዲቆጠር (እንዲፃፍ) ከአውግስጦስ ቄሳር ትዕዛዝ ወጣች፡፡ የእመቤታችን ጠባቂ የነበረው አረጋዊው ዮሴፍም ከዳዊት ወገን ነበርና ፀንሳ ከነበረችው ከድንግል ማርያም ጋር ሊቆጠር ከገሊላ ናዝሬት ከተማ ተነስቶ ቤተልሔም ወደምትባል ከተማ ሄደ፡፡ለሕዝብ ቆጠራ ከየአካባቢው የመጣው ሰው ቤተልሔም ከተማን ስለሞላት ፥ማደሪያው ቦታ ሁሉ በእንግዳ ስለተያዘ ቅድስት ድንግል ማርያምና ዮሴፍ ማደሪያ አላገኙም ነበር።**
**ስለዚህም በከብቶች ማደሪያ (በግርግም)ወይንም በበረት ለመጠለል ተገደዱ። ሌሊቱ በጣም ይበርድ ነበር ።**
**በዚያም ድንግል ማርያም የበኩር ልጇን ኢየሱስን ወለደችው።**
**„ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች“ የተባለው እውን ሆነ። (ኢሳ 7፡14)**
**ስሙን አማኑኤል አለችው፡፡ አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው፡፡**
**በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው (ኢሳ. ፱፥፪)፡፡**
**ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ እረኞች በዱር ሌሊት ከከብቶቻቸው ጋር ሆነው ሳለ የመላእክትን ዜናን ሰሙ ሌሊቱም (ጨለማውም ) ብርሃን ሆነ ።መላእክቱም ለእረኞቹ „እነሆ ለህዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ**



**ደስታ የምስራች እነግራችሁዋለሁና አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና.....“ሉቃ.2፤11**
**እረኞቹ መንጋ ጠባቂዎችም ፈሩ መላእኩም አትፍሩ „ በዳዊት ከተማ መድኅን ተወልዷል ይኸውም ብሩክ ጌታ ክርስቶስ ነው ምልክቱም ሕፃን አውራ ጣቱን ታስሮ በጨርቅ ተጠቀልሎ ታገኙታላችሁ !(ሉቃ 2፥8) ። እረኞቹም ከመላክት እንደተነገራቸው ሄደው ሲያዩ ህፃኑ ጌታችን ኢየሱስና እናቱን ቅድስት ድንግል ማርምን በከብት በረት አገኟቸው ፥ ሌሊቱ ብርድ(ውርጭ) ስለነበር የተወለደውን አምላክ እንስሳት ከበው በትንፋሻቸው ሲያሞቁት አዩ።**
**በዚህ በጌታችን ልደት ቀን መላእክትና የሰው ልጆች በአንድ ማኅበር፣ በአንድ ቃል ደስ በሏቸው „ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ስምረቱ ለሰብ ወሰላም በምድር“ "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ " ። እያሉ እግዚአብሔርን አመስግነዋል፡፡**
**በዚህ ታላቅ በዓላችን የምናደንቀው ሌላው ምሥጢር እግዚአብሔር ወልድ በቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀን፣ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና የመወለዱ ረቂቅ ምሥጢር ነው፡፡**

ቃላት
እረኛ = ጠባቂ
መንጋ =ብዙ ከብት (እንስሳት)
ታተመ = ተዘጋ
እንግዳ =አዲስ ሰው
ግርግም = ጉሮኖ (የበግ ማደሪያ)
በረት = የከብቶች ማደሪያ
ውርጭ = ብርድ
ረቂቅ = በጣም ትንሽ(ማይክሮ)
ገዥ = ባለስልጣን
በሥጋ ተገለጠ = ተወለደ
አማኑኤል = አግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው
አርአያም= ሰማይ
እውን= እውነት
ቤተልሔም= የዳቦ ቤት
አረጋዊ =ያረጀ ሰው
ውርጭ = ብርድ
ዱር = ሜዳ ወጭ
መድኅን መድኃኒት
**የበኩር ልጇን =የበኩር ልጇን የመጀመሪያ ልጇን**

# ሰብአ ሰገል (የጥበብ ሰዎች)

እግዚአብሔር ለአዳም በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ተሰቅዬ በሞቴ አድንኀለሁ ብሎ ቃል ገብቶለት ነበር መጽሐፈ ቀለሜንጦስ፡፡ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ሲወለድ ሰብአ ሰገል ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ ። ሰብአ ሰገል /ሦስቱ ነገሥታት የጥበብ ሰዎች/ ማንቱሲማር፣ በዲዳስፋ እና ሜልኩ የተባሉ የመጡት በኮከብ እየተመሩ ነበር።ኮከቡ የሚታየው ለነርሱ ብቻ ነበር ከተማ ሲገቡ አይታይም ነበር ፥ማንኛውም ኮከብ ሌሊት እንጂ በቀን አይታይም ይህ ይኽ ኮከብ ግን ቀን ቀን ይታያቸው ነበር ፥ የጥበብ ሰዎቹን በቀንና በሌሊት እየመራ ቤተልሔም ውስጥ አድርሷቸዋል።
ኢየሩሳሌም ከተማ ሲደርሱ ኢንዲህ ሲሉ ጠየቁ „ኮከቡን በምሥራቅ ዓይተን እንሰግድለት ዘንድ መጥተናልና ፥ የተወለደው ንጉሥ ወዴት ነው ?“ ብለው ። ሰብዓ ሰገል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም እንደሚወለድ እንጂ በየት ሥፍራ እንደሚወለድ አያውቁም ነበር።
ሄሮድስ ይኽን ቃል ሲሰማ እጅግ በመደናገጡና የኢየሱስ ክርስቶስም መወለድ ለሥልጣኑ እንደሚያሳስበው በመገመት ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ሕፃኑን ባገኛችሁት ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ በማለት (ሌላ ንጉሥ ሥጣኑን የሚወስድበት

ስለመሰለው)በሚሰጥር ሊገድለው አስቦ በሽንገላ አነጋገር ተናገራቸው። ሆኖም ግን ሰብዓ ሰገል ከኢየሩሳሌም እንደወጡ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ እየመራ ጌታችን እስከተወለደበት ስፍራ (ቤተልሔም) ድረስ አድርሷቸው ቆመ ።

የተወለደበት ቦታ ሲደርሱም በጣምም ደስ አላቸው ። ህፃኑን ኢየሱስን ከእናቱ ጋር አገኙ ወድቀውም ሰገዱለት ሳጥናቸውንም ከፍተው ስጦታቸውን (እጅ መንሻ አቀረቡለት) ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት ፡፡

ዕጣን፡- የተበረከተለት አንተ ያልተፈጠርክ ኋላም የማታልፍ አምላክ ነህ ሲሉ፡፡

ከርቤ፡- ያቀረቡለት አንተ የማትሞት ስትሆን ግን መራራ ሞትን ትቀበላለህ ሲሉ፡፡

ወርቅ፡- ያቀረቡለት አንተ የዓለሙ ሁሉ ገዥ ንጉሥ ነህ ሲሉ፡፡

ጌችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በ፵ኛው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ በመግባት የኦሪትን ሕግ ፈጽሟል ፡፡ሽማግሌው ስምዖን በጣም እረጅም ዓመት (ለሦስት መቶ ዓመታት) የጌታን መወለድ ከእግዚአብሔር ተነግሮት በቤተ መቅደሰ ሆኖ ሲጠባበቅ ነበር። በቅዱስ ወንጌል እንደ ተጻፈ በስምንተኛው ቀን እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ግዝረት ይፈጸምለት ዘንድ ፥ ሕፃኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት ። ይህም ቀን ጥር ፮ ሲሆን በዓለ ግዝረት ይባላል።

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ሰብአ ሰገል የሄሮድስን ትእዛዝ ሰምተው ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይመለሱ ሦስቱም አንድ ዓይነት ኅልም ማየታቸው ነው ። በኮከብ እየተመሩ ጌታ ከተወለደበት የደረሱት የጥበብ ሰዎች በሕልም ከእግዚአብሔር ተነግሯቸው ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ወደ መጡበት ስፍራ ተመልሰዋል።

ሰብአ ሰገል ከሄዱ በኋላ መልአክ ዮሴፍን ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ (ወደ ግብፅ ተሰደዱ)፥ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ። ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም ወደ ግብፅ ሄደ፥ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ። ማቴ.፪፡፲፫-፲፭

ከዚህም በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደ ተዘባበቱበት ባየ ጊዜ እጅግ ተቈጣና ጭፍራዎቹን ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን ልክ ሁለት ዓመት የሆናቸውንና፥ከዚያም የሚያንሱትን፥ በቤተ ልሔምና በአውራጃዎችዋ ሁሉ የነበሩትን ሕፃናት ፥ንጉሥ ይሆናል የተባልው ህጻን ይኖራል በማለት (ሄሮድስ ጌታችንን ያገኘ መስሎት) 144 ሺህ የቤቴልሔም ሕፃናትን አስገደለ።

ቃላት

ሰብአ ሰገል የግእዝ ቃል ነው= ሰብአ ማለት ሰው ሲሆን ሰገል ደግሞ ጥበብ ማለት ነው

በስውር ጠርቶ =በድብቅ አስጠርቶ

በሽንገላ አነጋገር =በውሸት (በማታለል)አነጋገር

እጅ መንሻ =የሚሰጥ ስጦታ

እጅ ነሳ =ከወገብ ጎንበስ ብሎ አከበረ

ጭፍራዎቹን =ወታደሮቹን

የማታልፍ =የማትሞት (ህይወቱ አለፍች =ሞተ)

በሌላ አቅጣጫ =በሌላ መንገድ

ሸሸ =አመለጠ፥ ተሰደደ

ተዘባበቱበት=ዋሹት



ቤተ ልሔም = ቤተ ኅብስት= የእንጀራ ቤት

## ኒቆዲሞስ

ኒቆዲሞስ የሚባል የአይሁድ መምህር ነበር፡፡ኒቆዲሞስ የፈሪሳውያን አለቃ ፣ የኦሪት መምህር ፣ የኦሪት አዋቂ ፣ ምሁር ፣ ሐብታምም ነበር፡፡በእርሱ ደረጃ የነበሩ ታላላቅ የአይሁድ ምሁራን መንፈሳዊ ስልጣናቸውና ሹመታቸው የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ረስተው በህዝቡ ላይ የሚመፃደቁ ነበሩ፡በዘመናቸው የጌታን መገለጥ አልወደዱትም፡፡ ስለዚህም ጌታችንን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምረውን ትምህርት በፍጹም አይቀበሉም ነበር ። እነርሱ በሥልጣናቸው ከመመጻደቅ የተነሳ ሕዝዝቡን ረስተውት ነበር ። ትዕቢተኞች፥ ሰውን የማይወዱ ትህትና የሌላቸው ሆነው ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ትህትናን ያስተምር ነበር ።ደግነትን ያስተምር ነበር።ሰውን መውደድ ያስተምር ነበር ።የተቸገረን መርዳት እንዳለብን ያስተምር ነበር ። የታመሙት ይፈውስ ነበር።

ጌታችንም ሲያስተምር የፈሪሳውያን ሀሳባቸው በግብዝነት የተሞላና ከንቱም እንደሆነ ይናገር ነበር፡፡ስለዚህ የኢየሱስን ትምህርት አይፈልጉትም አይወዱም ነበር፡፡ለደቀመዛሙርቱም ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ የሚበልጥ ሥራን እንዲሰሩ አስጠንቅቋቸዋል (ማቴ 5: 20 ማቴ 16:6)፡፡

ኒቆዲሞስ ግን ከእነዚህ ከፈሪሳዊያን መካከል የተገኘ ልዩ ምሁረ ኦሪት ነበር፡፡ ኒቆዲሞስ ራሱን ለእውነት ፣ ልቡን ለእምነት አዘጋጅቶ ከኹሉ ቀድሞ በሌሊት ክርስቶስን ፍለጋ የመጣ ፣ ከእነዚህ ፈሪሳዊያን ወገን ተለይቶ የክርስቶስን ትምህርት ለመማር ይመጣ ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የኒቆዲሞስን ትህትናውን ተቀብሎ ረቂቁን ምስጢረ ጥምቀትን አስተማረው ።

**ኒቆዲሞስም መምህር** ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን አለው።

**ኢየሱስም መልሶ።** እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።

**ኒቆዲሞስም**። ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው።

**ኢየሱስም መለሰ**፥ እንዲህ ሲል። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።ከሥጋ

የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ።

**ኒቆዲሞስ መልሶ።** ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለው።

**ኢየሱስም መልሶ እንዲህ** አለው። አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን?

ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?

ብሎ ምስጢረ ጥምቀት ሰማያዊ መሆንዋን ፥ስንጠመቅ ከእግዚአብሔር እንደምንወለድ እና በመንፈስ ልጅነትን እንደምናገኝ አስተማረው። መጀመሪያ ከእናትና አባት በሥጋ ፥ሁለተኛ በጥምቀት ከእግዚአብሔር በመንፈስ ። አንድ ክርስቲያን ሁለት ለደት አለው ማለት ነው።

## ጥያቄዎች

፩ ኒቆዲሞስ ከሌሎቹ የአሪት መምህራን በምን ይለያል ?
፪ የአይሁድ መምህራን ለምን የክርስቶስን ትምህርት አልወደዱም?
፫ ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ የሚሄደው መቼ ነበር ?
፬ ሁለተኛ መወለድ እንዴት ነው አብራራ?
፭ አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዴት ይገባል /ያያል/ ?
፮ አንድ ክርስቲያን ስንት ጊዜ ይወለዳል ?

# የጠፋው በግ

በጎች ሁል ጌዜ የሚሰማሩት አንድ ላይ ነው ፥ አንድ ላይ ሣር ይበላሉ፥አንድ ላይ ተሰብስበው ያድራሉ።እረኛው ደግሞ ጥሩ እና ለምለም ሣር ወደ አለበት ቦታ ይመራቸዋል ውኃም እንዲጠጡ ያደርጋል ።

አንድ ሰው አንድ መቶ በጎች ነበሩት ። ይህም ሰው በጎቹን ሲጠብቅ አንዱ ጠፋበት ወዴት ሄደ ? ፥ተኩላ በላው ፥ ገደል ገባ ፥ እያለ ብዙ ሰው ጠየቀ ማንም ሊነግርው አልቻለም። እርሱ ግን ፍለጋው

አላቆመም ፈልጎ ፈልጎ በመጠረሻ አገኘው ። በጣምም ደስ አለው ተሸከመውም ይዞትም አምጥቶ ወደ ዘጠና ዘጠኙ በጎች ቀላቀለው። ከዘጠና ዘጠኙ ካልጠፉት ይልቅ ጠፍቶ በተገኘው በግ ይህ ሰው ደስ አለው።ጎረቤቱም ሁሉ ጠርቶ የጠፋውን በጌን አገኘሁት ብሎ ደስታና ደግስ አድረገ።



ልጆች ! በበግ የተመሰለው አዳም ነው ወይንም ደግሞ እኛ የሰው ልጆች ነን ።በእረኛ (በበግ ባለቤት) የተመስልው ደግሞ ጌታችም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

በቅድሚያ አምላካችን ፲ ነገደ መላእክት ነበሩት ።አንዱ ሳጥናኤል የተባለው የመላእክት ነገድ ተእቢተኛ ነበር።በጣም ከመጥገቡም የተነሳ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ብሎ ተነሳ ።ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል አንተማ እንደኛ መላእክ ነህ እንጂ እግዚአብሔር አይደለኸም፥በፈጣሪህ አትዘብት ብለው ወደ ገሐነም አወረዱት ከሥልጣኑም ተሻረ ። ታዲዲያ ዘጠና ዘጠኝ ነገድ ቀሩ።አምላካችን አዳምን የፈጠረው ይህንን የጎደለውን ነገድ ለመሙላት ነበር።

ስለዚህ የተባረረው መልአክ ዲያቢሎስ ፥ ሰይጣን ፥ ሳጥናኤል ወዘተ ይባላል።ሁል ጌዜ አዳም በእርሱ ቦታ ስለገባ የአዳም ጠላት ነው ።ስለዚህም በገነት የነበርውን አዳምን አሳሳተው ከገነትም እንዲባረር አደረገ ።ጌታችን መድኃኒታችን /እረኛ/ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ አዳምን /በግ/ወደ ነበረበት ክብር ይመልሰው ዘንድ ፍለጋ መጣ ለአዳም ሲል በመስቀል ተሰቀለ ሞተ<< ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።>> ዮሐንስ 15:13:: ፥የማይሞተው አምላክ ሞተ፥ ሞት የተፈረደበትን አዳምን በሞቱ ነጻ አወጣው ።



አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠና ዘጠኙን መላእክት ትቶ አንዱን የጠፋውን አዳም ፍለጋ ወደ ዓለም መጣ።ከገነት ጫካዎች እስከ ጎልጎታ ፈለገው አገኘውም። ባገኘውም ጊዜም ደስ አለው ውርደትን አስወግዶ ፥በክብሩ አክብሮ፥ በቅድስና ቀድሶ ፥በይቅርታውና በሞቱ ሞትን ሽሮ ወደ ቀደመ ክብሩ መለሰው ከቅዱሳን ኅብረት ደመረው ። መላእክትም ደስ አላቸው

ጥያቄዎች

1 መላእክት የተፈጠሩት መቼ ነው ?
2 አዳም የተፈጥረው መቼ ነው ?
3 የመላክት ነገድ ስንት ነው?
4 ሳጥናኤል ለምን ተባረረ?
5 በሳጥናኤል ቦታ የተተካው ማን ነው ?
6 የጠፋው በግ በማን የመሰላል ?
7 ሳጥናኤልን በትዕቢቱ ከስልጣኑ ያባረሩት እነማን ናቸው ?

8 ሰይጣን ለምን የአዳም ጠላት የሆነ ይመስልሃል?

## ዔሳው እና ያዕቆብ

ይስሐቅም 40 ዓመት ሲሞላው ርብቃን አግብቶ ለ20 ዓመትም ያህል ልጅ ሳይወልዱ ኖሩ (መካን ነበረች)። ይስሐቅም 60 ዓመት በሆነው ጊዜ ርብቃ መንታ ልጆችን ፀነሰች ፥ሁለት ወንዶች ልጆችን ኤሳውንና ያዕቆብን ወለደች፡፡ እነርሱም በእናታቸው ማኅፀን ሳሉ ይጣሉ ነበር ከዚያም ሲወለዱም መጀመሪያ የተወለደው ኤሳው ነበር። ባደጉም ጊዜ ኤሳው አደን የሚያውቅ ሲሆን ያዕቆብ ከቤት የሚውል ሆነ፡፡ ይስሐቅም አርጅቶ ነበርና ኤሳው ከዱር አድኖ የሚያመጣለትን ስለሚመገብ ኤሳውን ይወደው ነበር፡፡ ርብቃም ደግሞ ከኤሳው ይልቅ ያዕቆብን ትወደው ስለነበር የምስር ወጥ ትሠራለት ነበር፡፡ አንድ ቀን ኤሳው አደን ውሎ እርቦት ደክሞት ምንምን ሳያድን (ሳያገኝ) ከዱር ሲመጣ ያዕቆብን ከምስር ወጡ እንዲሰጠው ለመነው፡ ፡ እርሱም ‹‹ብኩርናህን ስጠኝና ›› አለው፡፡ ኤሳውም እሺ እሰጥሃለሁ‹‹እኔ በርሃብ ከምሞት በኩር መሆን ምን ይጠቅመኛል? እሺ ውሰደው አለው ›› ያዕቆብም ብኩርናውን በመሐላ ካጸናለት በኋላ የምስር ወጡንም በእንጀራ አድርጎ ሰጠው፡፡ ኤሳውም በልቶ ጠጥቶ ሄደ፡፡ ይኸውም ኤሳው መብሉን ወዶ እልቅናውን ፥ሥልጣኑን፥ ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠ ፥ ብኵርናውን አቃለላት፡፡ ይስሐቅም አርጅቶ ዐይኖቹ ፈዘው የማያይ ከሆነ በኋላ ኤሳውን ጠርቶ ወደ በረሃ ሄዶ የሚወደውን ሥጋ አድኖ እንዲያመጣለት ላከው፡፡ ኤሳውም ወደ አደን ሲሄድ ርብቃ ታናሹን ልጇን ያዕቆብን ሁለት የበግ ጠቦቶችን አባቱ እንደሚወደው አድርጎ እንዲያዘጋጅና እንዲመረቅ(እንዲባረክ) ነገረችው፡፡ እርሷም የኤሳውን ልብስ አለበሰችው፡፡ ወደ አባቱም ገብቶ ምግቡን አቅርቦ ተመረቀ፤ በረከትንም ተቀበለ፡፡ ይስሐቅም ሲዳስሰው የኤሳውን ልብስ ለብሶ ስለነበር ያዕቆብ እንደሆነ አላወቀውም ነበር፡፡ ኤሳውም ለአባቱ አድኖ ያመጣውን ጣፋጭ መብል አዘጋጀ፥ ለአባቱም አቀረበ። አባቴ ተነሣ፥ ነፍስህም ትባርከኝ ዘንድ አድኜ ካመጣሁት ብላ አለው። ይስሐቅም፡- አንተ ማን ነህ? አለው፡፡ እርሱም፡- እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ አለው። ይስሐቅም፡- እጅግ ደነገጠ እንዲህም አለ፡- ያደነውን አደን ወደ እኔ ያመጣ ማን ነው? አንተ ሳትመጣም ከሁሉ በላሁ ባረክሁትም፤ እርሱም የተባረከ ሆኖ ይኖራል። ዔሳውም ፡-ይህንን በሰማ ጊዜ ታላቅ እጅግም መራራ ጩኸት ጮኸ ። አባቴ ሆይ፥ እኔንም ደግሞ ባርከኝ አለው። ይስሐቅም፡- ወንድምህ በተንኰል ገብቶ በረከትህን ወሰደብህ አለ። ዔሳውም፡- በእውነት ስሙ ያዕቆብ ተባለ፥ ሁለት ጊዜ አሰናከሎኛልና፤ ብኵርናዬን ወሰደ፥ አሁንም እነሆ በረከቴን ወሰደ። ደግሞም፡- ለእኔ በረከትን አላስቀረህልኝምን? አለ። ይስሐቅም፡- እነሆ፥ ጌታህ አደረግሁት፥ ወንድሞቹንም ሁሉ ለእርሱ ተገዦች ይሆኑ ዘንድ ሰጠሁት፥ በእህልም በወይንም አበረታሁት፤ ለአንተ ግን፥ ልጄ ሆይ፥ ምን ላድርግ? ዔሳውም፡- አባቴ ሆይ፥ በረከትህ አንዲት ብቻ ናትን? አባቴ ሆይ፥እኔንም ደግሞ ባርከኝ።ዔሳውም ቃሉን አንሥቶ አለቀሰ። ይስሐቅም ፡- እነሆ፥ መኖሪያህ ከምድር ስብ ከላይ ከሚገኝ ከሰማይም ጠል ይሆናል፤ በሰይፍህም ትኖራለህ፥ ለወንድምህም ትገዛለህ፤ ነገር ግን በተቃወምኸው ጊዜ ቀንበሩን ከአንገትህ ትጥላለህ።ዔሳውም አባቱ ስለ ባረከው በያዕቆብ ቂም ያዘበት፤ ርብቃም ይህን ስትሰማ ያዕቆብ በካራን ወደሚኖረው ወንድሟ ወደ ላባ ዘንድ ሄዶ የወንድሙ ቁጣ እስከበርድ በዚያ እንዲቀመጥ ነገረችው፡፡ ያዕቆብም ወንድሜ ቢከተለኝ፣ አውሬ ቢመጣብኝ እያለ እየፈራ ወደ ካራን ሄደ ሲመሽም ከአንድ ቦታ አድሮ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ፡፡ በዚያችም ሌሊት በራእይ አየ። የወርቅ መሰላል ተተክላ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሳ ቅዱሳን መላእክት በመሰላሏ ሲወጡባት ሲወርዱባት በላይዋ እግዚአብሔር ተቀምጦ አየ፡፡ ‹‹የአብርሃምና የይስሐቅ ፈጣሪ



እኔ ነኝና ወንድሜ ይገድለኛል እንደወጣሁም እቀራለሁ ብለህ አትፍራ እኔ በረድኤት ከአንተ ጋር ነኝ›› አለው፡፡ ይስሐቅም‹‹ይህቺ የሰማይ ደጅ ናት›› አለ። ትራስ አድርጎት የነበረውንም ድንጋይ አንስቶ ሐውልት አድርጎ ካቆማት በኋላ በራሷ ላይ ዘይት አፈሰሰባት፡፡ ብኩርና በዚያ ዘመን አንድ አባት ሲሞት አብዛኛው መሬትና ገንዘብ የሚሰጠው ለታላቁ ልጅ/ለበኩር/ ነበር። ይህ ውርስ ይባላል።ይህ ውርስ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጣቸውን ተስፋዎችም ይጨምር ነበር።ብኩርና ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሥልጣንም ነው ። ብኩርና ከእግዚአብሔር የተሰጠ በረከት እና ጸጋ ነው ።ብኩርና ሃይማኖት ነው።ኤሳው ግን ለጊዜው ስለራበው ይህንን ሁሉ የእግዚአብሔር ስጦታ በምስር ወጥ ለወጠው። የሚከተሉትን ቃላቶች አረፍተ ነገር ሥራባቸው

### ጥያቄ

ብኩርና ምን ይመስልሃል ?
ኤሳው ብኩርናውን በምስር ሲለውጥ ምን አጣ?
ኤስውቅ  የሚወደው ስራ ምን ነበር ?
ያዕቆብ ማለት ምን ማለት ነው ?

## ዮሴፍ (1)

እግዚአብሔርም ያዕቆብን አለው። ተነሥተህ ወደ ቤቴል ውጣ፥ በዚያም ኑር፤  እግዚአብሔርም   ከእንግዲህም ወዲህ ስምህ ያዕቆብ ተብሎ አይጠራ፥ ስምህ እስራኤል  ይባል እንጂ አለ፤ ስሙንም እስራኤል ብሎ ጠራው።

የያዕቆብ (እስራኤል) ልጆች   /፲፪ቱ የ፳ኤል ነገዶች/
ከልያ የወለዳቸው ልጆች፤ የያዕቆብ በኵር ልጅ **ሮቤል፥ ስምዖን፥ ሌዊ፥ ይሁዳ፥ ይሳኮር፥ ዛብሎን፤**
የከራሔል የወለዳቸው  ልጆች፤ **ዮሴፍ፥ ብንያም፤**
ከራሔል ባርያ ከባላ  የወለዳቸው ልጆች፤ **ዳን፥ ንፍታሌም፤**
ከልያ ባሪያ ከዘለፋ የወለዳቸው ልጆች፤  **ጋድ፥ አሴር፤**  እነዚህ በሁለቱ ወንዞች መካከል በሶርያ የተወለዱለት የያዕቆብ  ልጆች **በአጠቃላይ 12**  ናቸው።ያዕቆብም አባቱ በስደት በኖረበት አገር በከነዓን ምድር ተቀመጠ።
እስራኤልም ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር፥ እርሱ በሽምግልናው የወለደው ነበርና፤ በብዙ ኅብር ያጌጠችም ቀሚስ አደረገለት ።ወንድሞቹም አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንዲወደው ባዩ ጊዜ ወንድማቸውን  ጠሉት።
ዮሴፍም ሕልምን አለመ:-

እነሆ እኛ በእርሻ መካከል ነዶ ስናስር ነበርና፥ እነሆም፥ የእኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች፤ የእናንተም ነዶች በዙሪያ ከብበው እነሆ ለእኔ ነዶ ሰገዱ። ወንድሞቹም በእኛ ላይ ልትነግሥብን ይሆን? ወይስ ልትገዛ ይሆን?
አሉት። እንደ ገናም ስለ ሕልሙ  አብልጠው ይልቁን ጠሉት።

ደግሞም ሌላ ሕልምን አለመ :- እነሆ ደግሞ ሌላ ሕልምን አለምሁ፤ እነሆ ፀሐይና ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ። አባቱም ገሠጸው፥ እንዲህም አለው። ይህ ያለምኸው ሕልም ምንድር ነው? በውኑ እኔና እናትህ ወንድሞችህም መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?
ወንድሞቹም ቀኑበት አባቱ ግን ነገሩን ይጠብቀው ነበር። የእስራኤል ልጆች በዱር በጎችን ይጠብቁ ነበር።

አስራኤልም ለዮሴፍ ሄደህ በዱር ያሉትን ወንድሞችህን ደህና እነድሆኑ እይና ና ብሎ ላከው ።በሩቅ ሳለ አዩት። ወደ እነርሱም ገና ሳይቀርብ ገድለነው በጉድጓድ  እንጣለው ብለው ተማከሩ።  ክፉ አውሬም በላው እንላለን።

ሮቤልም ይህን ሰማ፥ ከእጃቸውም አዳነው፥ እንዲህም አለ። ሕይወቱን አናጥፋ።ደም አታፍስሱ፤ በዚህች ምድረ በዳ ባለችው ጉድጓድ ጣሉት፥ ነገር ግን አትግደሉት  አላቸው።ዮሴፍም ወደ ወንድሞቹ በቀረበ ጊዜ የለበሳትን በብዙ ኅብር ያጌጠቺቱን ቀሚሱን ገፈፉት፤ወስደውም ወደ ጉድጓድ ጣሉት፤ ጉድጓዱም ውኃ የሌለበት ደረቅ ነበረ።

ይሁዳም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው። ወንድማችንን ገድለን ደሙን ብንሸሽግ ጥቅማችን ምንድር ነው? ኑ፥ ለእስማኤላውያን እንሸጠው፥ ወንድማችን አንግደለው ሥጋችንም ነውና  ።እነርሱም ዮሴፍን አንሥተው ከጉድጓድ አወጡት፤ ለእስማኤላውያንም ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት፤ እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት። የዮሴፍንም ቀሚስ ወሰዱ፥ የፍየል አውራም አርደው ቀሚሱን በደም ነከሩት።

ብዙ ኅብር ያለበትን ቀሚሱንም   ለአባታቸውም አሳዩት፥ እንዲህም አሉት። ይህ የልጅህ ልብስ እንደ ሆነ ወይም እንዳልሆነ እስኪ እየው።እርሱም አውቆ። የልጄ ቀሚስ ነው፤ ክፉ አውሬ በልቶታል፤ ዮሴፍ በእርግጥ ተበጫጭቋል አለ።ያዕቆብም ለልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ።

ኅብር    የተለያየ ወቀለም ያለው
ነዶ     የእህል ዛላ
ገሠጻ   ተቆጣ
ገገፈፈ   አወለቀ (ልብሱን ወሰደ)
ሸሸገ    ደበቀ
አውራ   ትልቅ



ነዶ



# ዮሴፍ (2)

ዮሴፍ ግን ወደ ግብፅ ወረደ፤ የፈርዖን ጃንደረባ የዘበኞቹም አለቃ የሚሆን የግብፅ ሰው ጲጥፋራ ወደ ግብፅ ካወረዱት ከእስማኤላውያን እጅ ገዛው።እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ፤ በግብፃዊው ጌታውም ቤት ነበረ።ዮሴፍም በጌታው ፊት ሞገስን አገኘ፥ እርሱንም ያገለግለው ነበር፤ በቤቱም ላይ ሾመው፥ ያለውንም ሁሉ በእጁ ሰጠው ። የስውየው ሚስት ዮሴፍ ሊደፍረኝ ነው ብላ በውሸት ክሰሰችው ዮሰፍም ያንም በደል ሳይኖርበት ታሰረ።በእስር ቤት የነበሩት የግብፅ ንጉሥ ጠጅ አሳላፊና እንጀራ አበዛ ሁለቱም በአንዲት ሌሊት እንደ ሕልሙ ትርጓሜ እየራሳቸው ሕልምን አለሙ።ዮሴፍም ማልዶ ወደ እነርሱ ገባ፥ እነሆም አዝነው ሕልምን አልመን የሚተረጉምልን አጣን አሉት። ዮሴፍም አላቸው። ሕልምን የሚተረጉም እግዚአብሔር የሰጠው አይደለምን? እስቲ ንገሩኝ። የጠጅ አሳላፊዎች አለቃም ለዮሴፍ ሕልሙን እንዲህ ብሎ ነገረው። በሕልሜ የወይን ዛፍ በፊቴ ሆና አየሁ፥በዛፊቱም ሦስት አረግ አለባት፤ እርስዋም ቅጠልና አበባ አወጣች፥ ዘለላም አንጠለጠለች፥ የዘለላዋም ፍሬ በሰለ፤የፈርዖንም ጽዋ በእጄ ነበረ፤ ፍሬውንም ወስጄ በፈርዖን ጽዋ ጨመቅሁት፥ ጽዋውንም ለፈርዖን በእጁ ሰጠሁት።
ዮሴፍም አለው። የዚህ ትርጓሜው ይህ ነው፤ ሦስቱ አረግ ሦስት ቀን ነው፤ እስከ ሦስት ቀን ድረስ ፈርዖን ራስህን ከፍ ያደርጋል፥ ወደ ቀደመው ሹመትህም ይመልስሃል፤ ጠጅ አሳላፊ በነበርህበት ጊዜ ስታደርግ እንደ ነበረው እንደ ቀድሞው ሥርዓትም የፈርዖንን ጽዋ በእጁ ትሰጣለህ።ነገር ግን በጎ ነገር በተደረገልህ ጊዜ እኔን አስበኝ፥ ምሕረትንም አድርግልኝ፥ የእኔንም ነገር ለፈርዖን ነግረህ ከዚህ ቤት አውጣኝ፤
የእንጀራ አበዛዎቹ አለቃም ሕልሙን በመልካም እንደ ተረጎመ ባየ ጊዜ ዮሴፍን እንዲህ አለው። እኔም ደግሞ ሕልም አይቼ ነበር፥ እነሆም ሦስት መሶብ ነጭ እንጀራ በራሴ ላይ ነበረ፤በላይኛውም መሶብ ፈርዖን ከሚበላው ከጋጋሪዎች ሥራ ሁሉ ነበረበት፤ ወፎችም በራሴ ላይ ከመሶቡ ይበሉ ነበር።ዮሴፍም መልሶ እንዲህ አለው። የዚህ ትርጓሜው ይህ ነው፤ ሦስቱ መሶብ ሦስት ቀን ነው፤እስከ ሦስት ቀን ድረስ ፈርዖን ራስህን ከፍ ያደርጋል፥ በእንጨትም ላይ ይሰቅልሃል፤ ወፎችም ሥጋህን ይበሉታል።
በሦስተኛውም ቀን ፈርዖን የተወለደበት ቀን ነበረ፥ ለሠራዊቱም ሁሉ ግብር አደረገ፤ የጠጅ አሳላፊዎቹን አለቃና የእንጀራ አበዛዎቹን አለቃ በአሽከሮቹ መካከል ከፍ አደረገ።የጠጅ አሳለፊዎቹንም አለቃ ወደ ስፍራው መለሰው፥ ጽዋውንም በፈርዖን እጅ ሰጠ፤የእንጀራ አበዛዎቹንም አለቃ ሰቀለው፥ ዮሴፍ እንደተረጎመላቸው።የጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ግን ዮሴፍን አላሰበውም፥ ረሳው እንጂ።
ከሁለት ዓመት በኋላም ፈርዖን ሕልምን አየ፥ እነሆም፥ በወንዙ ዳር ቆሞ ነበር።
እነሆም፥ መልካቸው ያማረ ሥጋቸውም የወፈረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጡ፥ በውኃውም ዳር በመስኩ ይሰማሩ ነበር።
ከእነርሱም በኋላ እነሆ መልካቸው የከፋ ሥጋቸውም የከሳ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዝ ወጡ፥ በእነዚያም ላሞች አጠገብ በወንዙ ዳር ይቆሙ ነበር።
መልካቸው የከፋ ሥጋቸውም የከሳ እነዚያም ላሞች መልካቸው ያማረውን ሥጋቸው የወፈረውን ሰባቱን ላሞች ዋጡአቸው። ፈርዖንም ነቃ።
ደግሞም ተኛ ሁለተኛም ሕልምን አየ። እነሆም በአንድ አገዳ ላይ የነበሩ ያማሩና መልካም የሆኑ ሰባት እሸቶች ወጡ፤እነሆም ከእነርሱ በኋላ የሰለቱና በምሥራቅ ነፋስ የተመቱ ሰባት እሸቶች ወጡ፤የሰለቱትም እሸቶች ሰባቱን ያማሩና የዳበሩ እሸቶች ዋጡአቸው።ፈርዖንም ነቃ፥ እነሆም ሕልም ነበረ። በነጋም ጊዜ ነፍሱ ታወከችበት፤ ወደ ሕልም ተርጓሚዎች ሁሉ ወደ ግብፅ ጠቢባንም ሁሉ ልኮ ወደ እርሱ ጠራቸው፤ ፈርዖንም ሕልሙን ነገራቸው፥ ነገር ግን ከእነርሱ ለፈርዖን የሚተረጉም አልተገኘም።

የዚያን ጊዜ የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ዮሴፍን አስታሰው ለፈር ኦን ስለ ዮሴፍ ህልም እንደሚፈታ ነገረው ። ፈርዖንም ልኮ ዮሴፍን አስጠራ፥ ከግዞት ቤትም አስቸኰሉት፤ እርሱም ተላጨ፥ ልብሱንም ለወጠ፥ ወደ ፈርዖንም ገባ።
ዮሴፍም ፈርዖንን አለው። የፈርዖን ሕልሙ አንድ ነው፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ያለውን ለፈርዖን ነግሮታል።ሰባቱ መልካካሞች ላሞች ሰባት ዓመታት ናቸው፥ ሰባቱም መልካካሞች እሸቶች ሰባት ዓመታት ናቸው፤ ሕልሙ አንድ ነው።ከእነርሱም በኋላ የወጡት የከሱትና መልከ ክፉዎቹ ሰባት ላሞች ሰባት ዓመታት ናቸው፥ የሰለቱትና የምሥራቅ ነፋስ የመታቸው ሰባቱም እሸቶች እነርሱ ራብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ናቸው።ፈርዖን የነገርሁት ነገር ይህ ነው እግዚአብሔር ሊያደርገው ያለውን ለፈርዖን አሳየው ።
እነሆ በግብፅ ምድር ሁሉ እጅግ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ፤ደግሞ ከዚህ በኋላ የሰባት ዓመት ራብ ይመጣል፥ በግብፅ አገር የነበረውም ጥጋብ ሁሉ ይረሳል፤ ራብም ምድርን በጣም ያጠፋል፤
በኋላ ከሚሆነው ከዚያ ራብ የተነሣም በምድር የሆነው ጥጋብ አይታወቅም፥ እጅግ ጽኑ ይሆናልና። ሕልሙም ለፈርዖን ደጋግሞ መታየቱ ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ ስለ ሆነ ነው፥ እግዚአብሔርም ፈጥኖ ያደርገዋል።አሁንም ፈርዖን ብልህና አዋቂ ሰውን ይፈልግ፥ በግብፅ ምድር ላይም ይሹመው። ፈርዖንም ዮሴፍን አለው። እንደ አንተ ያለ ብልህ አዋቂም ሰው የለም፥ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ገልጦልሃልና።ፈርዖንም ዮሴፍን። በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ሾምሁህ አለው።ፈርዖን ቀለበቱን ከእጁ አወለቀ በዮሴፍ እጅም አደረገው፥ ነጭ የተልባ እግር ልብስንም አለበሰው፥ በአንገቱም የወርቅ ዝርግፍን አደረገለት።

# ዮሴፍ(3)

ዮሴፍም የግብፅ ንጉሥ የፈርዖን ህልም ሲፈታ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበረ። ዮሴፍ ከተሾመ በኋላ የግብፅን ምድርንም ሁሉ ዞረ።በሰባቱም በጥጋብ ዓመታት የምድሪቱ ፍሬ ክምር ሆነ።ዮሴፍም እንደ ባሕር አሸዋ እጅግ ብዙ የሆነ ስንዴን አከማቸ። ሚስት አግብቶ ሁለት ልጆች ተወለዱለት።ዮሴፍም የበኵር ልጁን ስም ምናሴ ብሎ ጠራው፥ እንዲህ ሲል። እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ የአባቴንም ቤት አስረሳኝ፤የሁለተኛውንም ስም ኤፍሬም ብሎ ጠራው፥ እንዲህ ሲል። እግዚአብሔር በመከራዬ አገር አፈራኝ።  በግብፅ ምድር የነበረውም የሰባቱ ዓመት ጥጋብ አለፈ፥የግብፅ ምድርም ሁሉ ተራበ። በምድርም ሁሉ ላይ ራብ ሆነ፤ ዮሴፍም እህል ያለበትን ጎተራ ሁሉ ከፍቶ ለግብፅ ሰዎች ሁሉ ይሸጥ ነበር። አገሮችም ሁሉ እህል ይገዙ ዘንድ ወደ ግብፅ ወደ ዮሴፍ መጡ፤ በምድር ሁሉ ራብ እጅግ ጸንቶ ነበርና ። ያዕቆብም በግብፅ እህል እንዳለ ሰማ፥ ያዕቆብም ልጆቹን ወደዚያ ሂዱ፥ እንድንድንና እንዳንሞትም ከዚያ ስንዴ ሸምቱልን ብሎ ወደ ግብፅ ላካቸው ።የዮሴፍን ወንድም ብንያምን ግን ያዕቆብ ከወንድሞቹ ጋር አላከውም ።
ዮሴፍም በምድር ላይ ገዥ ነበረ፥ እርሱም ለምድር ሁሉ ስንዴ ይሸጥ ነበር፤ የዮሴፍም ወንድሞች በመጡ ጊዜ ለዮሴፍ በምድር ላይ በግምባራቸው ሰገዱለት።እናንተ ከወዴት መጣችሁ? አላቸው። እነርሱም። ከከነዓን ምድር እህል ልንሸምት የመጣን ነን አሉት። ዮሴፍም ወንድሞቹን አወቃቸው፥ እነርሱ ግን አላወቁትም፤ዮሴፍም ስለ እነርሱ አይቶት የነበረውን ሕልም አሰበ።



እንዲህም አላቸው። እናንተ ሰላዮች ናችሁ፤አላቸው።እነርሱም ጌታችን ሆይ አይደለም፤ ባሪያዎችህ እኛ ስንዴ ልንገዛ ነው የመጣነው ። እኛ ሁላችን የአንድ ሰው ልጆች ነን፤ እኛ እውነተኞች ነን፥ ታናሹም እነሆ ዛሬ ከአባታችን ጋር ነው፥ አንዱም ጠፍቶአል። ሰላዮች አይደለንም።
ዮሴፍም አላቸው። እናንተ ሰላዮች ናችሁ ብዬ የተናገርኋችሁ ይህ ነው፤በዚህ ትፈተናላችሁ፤ ታናሽ ወንድማችሁ ካልመጣ በቀር ከዚህ አትወጡም።እውነትን የምትናገሩ ከሆነ ነገራችሁ ይፈተን ዘንድ ከእናንተ አንዱን ላኩ፥ ወንድማችሁንም ይዞ ይምጣ እናንተም ታሥራችሁ ተቀመጡ፤ ይህ ካልሆነ የፈርዖንን ሕይወት ሰላዮች ናችሁ። ሦስት ቀን ያህል እስር ቤት ጨመራቸው።
በሦስተኛውም ቀን ዮሴፍ እንዲህ አላቸው። ትድኑ ዘንድ ይህን አድርጉ፤ እኔ እግዚአብሔርን እፈራለሁና።
እናንተ የታመናችሁ ከሆናችሁ ከእናንተ አንዱ ወንድማችሁ በእስር ቤት ይታሰር እናንተ ግን ሂዱ፥ እህሉንም (ስንዴ) ለቤታችሁ ውሰዱ፤ታናሹንም ወንድማችሁን ወደ እኔ ይዛችሁ ኑ፤ ነገራችሁም የታመነ ይሆናልና አትሞቱም። እንዲህም አደረጉ።እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ። በእውነት ወንድማችንን(ዮሴፍ) በድለናል፥ እኛን ሲማጸን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አልሰማነውምና፤ ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን።
ሮቤልም መልሶ እንዲህ አላቸው። ብላቴናውን (ዮሴፍ)አትበድሉ ብያችሁ አልነበረምን? እኔም አልሰማችሁኝም፤ ስለዚህ እነሆ አሁን ደሙ ይፈላለገናል። እነርሱም ዮሴፍ የሚያወሩትን እንደሚሰማባቸው አላወቁም፥ በመካከላቸው አስተርጓሚ ነበረና። ከእነርሱም ዘወር ብሎ አለቀሰ፤ ደግሞም ወደ እነርሱ ተመልሶ ተናገራቸው፥ ስምዖንንም ከእነርሱ ለይቶ ወሰዶ በፊታቸው አሰረው።
ዮሴፍም የእህል መያዣቸውን እህል ይሞሉት ዘንድ አዘዘ፤ የእየራሳቸውንም ብር በየእህል መያዣቸው ይመልሱት ዘንድ ደግሞም የመንገድ ስንቅ ይሰጡአቸው ዘንድ አዘዘ። እንዲሁም ተደረገላቸው።
እነርሱም እህሉን በአህዮቻቸው ላይ ጫኑ፥ ከዚያም ተነሥተው ሄዱ።ከእነርሱም አንዱ ባደሩበት ስፍራ ለአህያው ገፈራን ይሰጥ ዘንድ የእህል መያዣውን ሲፈታ ብሩን አየ። ለወንድሞቹም ነገራቸው። ልባቸውም ደነገጠ፥ እየተንቀጠቀጡም እርስ በርሳቸው ተባባሉ። እግዚአብሔር ያደረገብን ይህ ምንድር ነው?

# ሙሴ(1) ፳ኤል በግብጽ

ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የገቡት የእስራኤል ልጆች ስሞች እነዚህ ናቸው፤ ሰው ሁሉ ከቤተ ሰቡ ጋር ገባ።ሮቤል፥ስምዖን፥ ሌዊ፥ ይሁዳ፥ ይሳኮር፥ ዛብሎን፥ብንያም፥ ዳን፥ ንፍታሌም፥ ጋድ፥ አሴር። ያዕቆብም ወደ ግብፅ ሲሄድ አብረውት የሄዱት ልጆቹና ዘመደቹ በጠቅላላው 70 ነበሩ።ዮሴፍም አስቀድሞ በግብፅ ነበረ።ዮሴፍም ሞተ፥ ወንድሞቹም፥ ሁሉ አለፉ።የእስራኤልም ልጆች ተዋለዱ፥ እጅግም በዙ፥ ምድሪቱም በእነርሱ ሞላች።

በግብፅም ዮሴፍን ያላወቀ አዲስ ንጉሥ ተነሣ።ዮሴፍ ለግብፅ ያደረገው ውለታ ተረሣ።ስለዚህም ግብፆች እስራኤላውንን በመከራ እንዲግዟቸው ባሪያ እንዲያደርጓቸው ሕግ አወጡ።የእስራኤል ዘራቸው እንዲጠፋ ወንድ ልጅ ሲወለድ አዋላጆች ህጻናቱን እንዲገድሉ ከግብፅ ንጉሥ ተእዛዝ ወጣ።አዋላጆች ግን እግዚአብሔርን ፈርተው እኛ ልናዋልድ ስንገሄድ አንርሱ ቀድመው ወልደው እናገኛቸዋለን አሉ።ንጉሡ ፈርኦን ሌላ ሕግ አወጣ ይኸውም የሚወለደውን የእብራውያን ወንድ ልጅ ሁሉ ወደ ወንዝ እንዲጣል ትእዛዝ አወጣ።

በዚህ ወቅት ከሌዊ ወገን አንድ ሰው ሄዶ የሌዊን ልጅ አገባ። ወንድ ልጅም ወለደች ሦሥስት ወር ሸሸገችው በመጨረሻም ሳይታወቅ በሳጥን አድርጋ በወንዝ ዳር ባለው ጫካ ውስጥ ወንዙ ዳር ላይ ለቀቀችው እህቱ ማርያምም የሚሆነውን ትከታተል ነበረ።የፈርኦን ልጅ ልትታጥብ ወደ ወንዝ ወርዳ ሳለ ሳጥኑን በወንዙ ዳር አየችው ። አገልጋይዋንም ልካ አስመጣችው። ሳጥኑን ስትከፍትም ህጻኑ እያለቀሰ አየችው አዘነችለትም።

እህቱም ማርያምም የንጉሡ ልጅ እንዳነሳችው ባየች ጊዜ ሄዳ የምታጠባ ከእብራውያን ወገን ሴት እኔ ላምጣልሽ አለቻት ።ሄዳም በምጢር እናቱን አመጣችላት። የፍርኦን ልጅም ይህንን ልጅ ከወንዝ አገኘሁት አጥቢልኝ ገንዝብ እከፍልሻለሁ ብላ ከልጁ እናት ጋር ተስማማች። እናቱም ህጻኑን ጡት እያጠባች በድብቅ ስለ እምነቱና ስለ ሀገሩ



እያስተማረች አሳደገችው። ሕፃኑም አደገ፥ የንጉሡም ልጅ ወደ ፈርዖንም ልጅ ዘንድ አመጣችው፥ ለእርስዋም ልጅ ሆነላት። እኔ ከውኃ አውጥቼዋለሁና ስትልም ስሙን ሙሴ ብላ ጠራችው።
ወቅቱ ግብፆች በእብራውያን ላይ መከራ የሚያበዙበት ነበር ።ሥራ ያለረፍት ያሠሯቸው ነበር፥ አንድ ሰው ቢታመም እንኳን በሥራ ላይ እያለ ይሞታል።ሴት እርጉዝ ሆና በሥራ ላይ እያለች ትወልድ ነበር። በአጠቃላይ እብራውያን (እስራኤላውያን) እንደ ሰው አይቆጠሩም ነበር።ሙሴም በንጉሥ ቤት የንጉሥ ልጅ ተብሎ አደገ። እርሱ ግን ግብፃዊ አልነበረም እናቱ ስለ እምነቱና ዕብራዊ እንደሆነ ከልጅነት ጀምሮ ስላስተማረችው በእምነቱና በማንነቱ ጸና።

በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ፤ ሙሴ በጎረመሰ ጊዜ ወደ ወንድሞቹ ወደ እብራውያን ወጣ፥የሥራቸውንም መከራ ተመለከተ፤ የግብፅም ሰው የወንድሞቹን የዕብራውያንን ሰው ሲመታ አየ።ወዲህና ወዲያም ተመለከተ፥ ማንንም አላየም፥ ግብፃዊውንም ገደለ፥ በአሸዋም ውስጥ ሸሸገው።በሁለተኛውም ቀን ወጣ፥ ሁለቱም የዕብራውያን ሰዎች ሲጣሉ አየ፤ በዳዩንም ለምን ባልንጀራህን ትመታዋለህ? አለው። አንደኛው በእኛ ላይ አንተን አለቃ ወይስ ዳኛ ማን አደረገህ? ወይስ ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትሻለህን? አለው። ሙሴም። በእውነት ይህ ነገር ታውቆአል ብሎ ፈራ።ፈርዖንም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ። ሙሴ ግን ከፈርዖን ፊት ኰበለለ፥ በምድያምም ምድር ተቀመጠ፤ በውኃም ጕድጓድ አጠገብ ዐረፈ።

# ሙሴ (ክፍል2)

ሙሴም ከፈርኦን ፊት ከኮበለለ በኋላ በምድያም ምድር ተቀመጠ በወኃ ጉድጓድ አጠገብ ዐረፈ።የምድያም ካህን የዮቶር ሴት ልጆች በጎቻቸውን ውኃ ሲያጠጡ ሌሎች እረኞች ሲገፏቸው አይቶ ረዳቸው ።ሴቶቹም ሄደው ለአባታቸው ነገሩት ። አባታቸው ዮቶር /ራጉኤል/ ወደ ቤት አምጡት አላቸው።ወደ ዮቶር ቤት ገባ ። ሙሴም ከዮቶር ጋር መቀጥ ወደደ። ሲታራ የምትባል ሴት ልጁን አጋባው አብረው መኖር ጀመሩ።

ሙሴም የዮቶርን የአማቱን የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር፤ ወደ ምድረ በዳ ዳርቻም በጎቹን ነዳ፥ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ።የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ(ሐመልማል) መካከል ታየው፤ እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ።ሙሴም ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ። ይህች እሳት የሚነድባት ሳትቃጥል ለምለም ሆና የቀረችው ቁጥቋጦ እጸ ጳጦስ ትባላለች ። እግዚአብሔርም እርሱን ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ።ሙሴ ሆይ ብሎ ወደዚህ አትቅረብ አለው። አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው። እኔ የአባቶችህ ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው።

እናቱ ጡት እያጠባች ባስተማረችው እምነት ብቻ ሙሴ እግዚአብሔርን አመነ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ።እግዚአብሔርም አለ። በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ ጩኸታቸውን ሰማሁ፤ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ፤ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ፥ አንተን መርጬሐለሁ ብሎ ነገረ ። አሁንም ና፥ ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ።

ሙሴም እግዚአብሔርን። ወደ ፈርዖን የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ? አለው።በእውነት እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ ኃይልን እስጥሃለሁ ፈርዖንን እንድታስፈራው እንድታስጨንቀው አደርግሃለሁ አለው። ሙሴም መለሰ። እነሆ አያምኑኝም ቃሌንም አይሰሙም። እግዚአብሔር ከቶ አልተገለጠልህም ይሉኛል አለ። እግዚአብሔርም ሙሴን በትርህን ወደ መሬት ጣላት አለው፤ እርሱም በመሬት ጣላት፥ እባብም ሆነች፤ ሙሴም ከእርሷ ሸሸ። እግዚአብሔርም ሙሴን። የአባቶቻቸው አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ፥ እግዚአብሔር እንደ ተገለጠልህ እንዲያምኑ እጅህን ዘርግተህ ጅራትዋን ያዝ አለው። እጁንም ዘርግቶ ያዛት በእጁም ውስጥ በትር ሆነች።

እግዚአብሔርም ደግሞ። እጅህን ወደ ብብትህ አግባ አለው። እጁንም ወደ ብብቱ አገባት፤ ባወጣትም ጊዜ እነሆ፥ እጁ እንደ በረዶ ለምጽ ሆነች።እርሱም። እጅህን ወደ ብብትህ መልስ አለው። እጁንም ወደ ብብቱ መለሳት፥ ከብብቱም ባወጣት ጊዜ እነሆ ተመልሳ ገላውን መሰለች።ደግሞም አለው። እንዲህም ይሆናል፤ ባያምኑህ የፊተኛይቱንም ምልክት ነገር ባይሰሙ፥ የሁለተኛይቱን ምልክት ነገር ያምናሉ።



ጌታ ሆይ፥ እኔ አፌ ኰልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ፤ ትናንት ከትናንት ወዲያ ባሪያህንም ከተናገርኸኝ ጀምሮ አፈ ትብ ሰው አይደለሁም።እግዚአብሔርም። የሰውን አፍ የፈጠረ ማን ነው? ዲዳስ ደንቆሮስ የሚያይስ ዕውርስ ያደረገ ማን ነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን?ሌዋዊው ወንድምህ አሮን እርሱ እንዲናገር አውቃለሁ፤ እነሆም ደግሞ ሊገናኝህ ይመጣል፤ ባየህም ጊዜ በልቡ ደስ ይለዋል። አንተም ትናገረዋለህ ቃሉንም በአፉ ታደርገዋለህ፤ እኔ ከአፍህና ከአፉ ጋር እሆናለሁ፥ የምታደርጉትንም አስተምራችኋለሁ። ሙሴም ከእግዚአብሔር ለሁሉም ጥያቄ መልስ ስላገኘ ፤ አንተ ከኔ ጋር ከሆንክ እሺ ብሎ፤ ዕብራውያንን ከፈርዖን የግፍ አገዛዝ ለማላቀቅ ፤ተአምራትን የሚያደርግባትን በትር በእጁ ይዞ ወደ ግብፅ ሄደ።



## ሙሴ (ክፍል3)

ሙሴም አማቱን ዮቶርን አስፈቅዶ ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ግብጽ ወደ ወንድሞቹ ወደ ወገኖቹ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም ሄደ ወደ ግብጽም ሲሄድ ከወንድሙ አሮን ጋር ተገናኘ ።በትሩንም ይዞ ነበር ።ሙሴም አፉ ኮልታፋ በደንብ መናገር ስለማይችል በርሱ ምትክ አሮን ይናገር ነበር።

ሙሴና አሮን ሕዝቡንና የእ፳ኤልን ሽማግሌዎችን ሁሉ ሰበሰቡ አሮንም አግዚአብሔር ለሙሴ የነገረውን ቃል ተናገረ ሙሴም ተዐምራቱን በሕዝቡ ፊት አደረገ።ሕዝቡም ሙሴ ነጻ ሊያወጣቸው እንደመጣ አግዚአብሐርም የእ፳ኤልን ልጆች እንደጎበኘ ጭንቀታቸውንም እንዳየ ተረዱ ለእግዚአብሔርም አጎነበሱ ሰገዱ ።

ከዚህ በሁኋላ ሙሴና ዐሮን መጥተው ፈርዖንን አንዲህ አሉት። የእ፳ኤል አምላክ እግዚአብሔር አንዲህ ይላል። በምድረበዳ በዓል ያደርጉልኝ ዘንድ ሕይበን ልቀቅ። ፈርዖንም ቃሉን አሰማ ዘንድ እስራኤልን አለቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው ?

## እግዚአብሐሔርን አላውቅም ፳ኤልንም አልቅም አለ። እግዚአብሐሔር የፈርዖንን ልብ አደንድኖ ሕዝቡን ለመልቀቅ እምቢ ስለአለ የሚከተሉትን ፲ መቅሰፍቶች በግብጽ ላይ አወረደ።

### ፩ ውኃ ወደም መለወጥ

(ኦሪት ዘጸአት ፯፥፲፱) እግዚአብሐሔር ሙሴን አለው አሮንን በትርህን ውሰድ በግብፅም ወንዞችና ጅረቶችዋ ላይ በዱር በወይራ ዘይትና በዕቃዎቻቸው ሁሉ በግብፅም አገር ሁሉ በእንጨት ዕቃዎች ውስጥ በድንጋይም ዕቃ ሁሉ ደም ይሆናል አለ።

### ፪ ጓጉንቸር

(ኦሪት ዘጸአት ፰፥፪) ሕይቤን ለመልቀቅ እንቢ ብትል ግን እነሆ እኔ አገርህን ሁሉ በጓጉንቸሮች እመታለሁ;
ወንዙም ጓጉንቸሮችን ያፈላል ወጥተውም ወደ ቤትህ ወደ አልጋህ በሁሉ ቦታ ይሆናሉ።

### ፫ ቅማል

(ኦሪት ዘጸአት፰፥፲፮) እግዚአብሐሔርም ሙሴን አለው አሮንን በትርህን ዘር በግብፅም አገር ሁሉ ቅማል እንዲሆን የምድሩን ትቢያ ምታ በለው ።

### ፬ ተናካሽ ዝንብ

(ኦሪት ዘጸአት፰፥፳፩) ሕዝቤን ባትለቅክ በአንተ ላይ በባሪያዎችህም በሕዝብህም በቤቶችህም ላይ የዝንብ መንጋዎችን እሰድዳለሁ።

### ፭ የእንሣት እልቂት

(ኦሪት ዘጸአት ፱፥፫) እነሆ የእግዚአብሐሔር እጅ በአህያዎቹም በግመሎችም በበሬዎችም በበጎችም ላይ ትሆናለች ታላቅ
ችግር ይሠራል በአህያዎቹም በግመሎችም በበሬዎችም በበጎችም ላይ ትሆናለች ታላቅ ችግር ይሠራል።



### ፮ ቁስል

(ኦሪት ዘጸአት፱፥፰)እግዚአብሐሔርም ሙሴንና አሮንን እጃችሁን ሞልታችሁ ከምድጃ አመድ ውሰዱ ሙሴም በፈርዖን ፊት ወደ ሰማይ ይበትነው በግብፅም አገር ሁሉ በሰውና
በእንስሳ ላይ ቍስል ይሆናል።

### ፯ በረዶ

(ኦሪት ዘጸአት ፱፥፲፰) እነሆ ነገ በዚህች ሰዓት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በግብፅ እጅግ ታላቅ በረዶ አዘንብብሃለሁ

### ፰ የአንበጣ መንጋ

(ኦሪት ዘፀአት ፲፥፬) ሕዝቤን ለመልቀቅ እንቢ ብትል ግን፥ እነሆ ነገ በአገርህ አንበጣዎችን አመጣለሁ፤ የምድሩንም ፊት ይሸፍኑታልና ምድሩን ለማየት አይቻልም፤

### ፱ ጨለማ

(ኦሪት ዘጸአት ፲፥፳፩) እግዚአብሐሔርም ሙሴን እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ በግብፅም አገር ላይ ፅኑ ጨለማ ይሁን

**፲ የበኩር ልጅ ሞት** (ኦሪት ዘጸአት ፲፪፥፩) ሞተ በኩር ቅጣት በግብጽ ሲመጣ ፈርዖን አጁን ሰጠ የእስራኤልንም ሕዝብ አንዲለቅ ተገደደ ።አንዲህም ሆነ እግዚአብሐሔርም በግብፅ አገር ሙሴንና አሮንን



እንዲህ ብሎ ተናገራቸው ሁሉም ለአባቱ ቤት አንድ የበግ ጠቦት፥ ለአንድ ቤትም አንድ ጠቦት ይውሰድ።፤ እያንዳንዱም እንደሚበላው መጠን ከጠቦቱ ይካፈሉ። የእስራኤልም ማኅበር ጉባኤ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት።ደሙም ወስደው በሚበሉበት ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን ይቅቡት።እኔም በዚያች ሌሊት በግብፅ አገር አልፋለሁ፥ በግብፅም አገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኵርን ሁሉ እገድላለሁ፤ ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፤ ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ(ማንንም አልገድልም)።ይህም ቀን መታሰቢያ ይሁናችሁ(ፋሲካ)፥ ለእግዚአብሐሔርም በዓል ታደርጉታላችሁ፤ ለልጅ ልጃችሁ ሥርዓት ሆኖ ለዘላለም ታደርጉታላችሁ።
እኩለ ሌሊት በሆነ ጊዜ እግዚአብሐሔር፥ በዙፋን ከተቀመጠው ከፈርዖን በኵር ጀምሮ የግብፃውያንን በግብፅ ምድር የተገኘውን በኵር ሁሉ፥ የእንስሳውንም በኵሮች ሁሉ መታ(ገደለ)።ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን በሌሊት ጠርቶ። እናንተ የእስራኤልም ልጆች ተነሡ፥ ከሕዝቤ መካከል ውጡ፤ ሂዱም አላቸው። አነርሱም ያላቸውን ንብረት ሁሉ ይዘው ከግብጽ ውጡ። ይህች ሌሊት በእስራኤል ልጆች ሁሉ ዘንድ እስከ ልጅ ልጃቸው ድረስ ለእግዚአብሐሔር የተጠበቀች የበዓላቸውም ቀን ናት ።እግዚአብሐሔርም ሙሴንና አሮንን አለ። ይህ የፋሲካ ሕግ ነው።የእስራኤልም ልጆች በግብፅ ምድር የተቀመጡት ዘመን አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ነው።

# ቀይ ባሕርን መሻገር

እስራኤላውያን በእግዚአብሐሔር ኃይል በሙሴም መሪነት ከግብጽ ወጥተው ወደ ከነዓን ጉዞ ጀመሩ፡፡ የኤርትራ ባሕር ጉዟቸውን ስለገታው በባሕሩ ዳርቻ ሰፈሩ፡፡ ፈርዖን በሕዝቡ ነጻ መውጣት ተቆጥቶ በፈረስና በሠረገላ ሠራዊቱን ላከ፡፡ የፈርዖን ወታደሮች እስራኤላውያንን በማሳደድ ተከተሏቸው፡፡ በኤርትራ ባሕር አጠገብ ሰፍረው አዩዋቸው፡፡ የእስራኤል ልጆችም ግብጻውያንንና ስድስት መቶ ሰረገላዎቻቸውን ፈረሶቻቸውንም ባዩ ጊዜ ደነገጡ፤ ወደ እግዚአብሐሔርም ጮኹ፡፡
ሙሴንም "በግብጽ መቃብር ስላልኖረ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ አወጣኸንን? በምድረ በዳ ከምንሞት ብንገዛላቸው ይሻል ነበር" አሉት፡፡ ሙሴ ለሕዝቡ "አትፍሩ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብጻውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ፤ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሐሔርን ማዳን እዩ፡፡ እግዚአብሐሔር ስለ እናንተ ይዋጋል እናንተም ዝም ትላላችሁ፡፡" አላቸው፡፡
እግዚአብሐሔር መልአኩን ላከ፡፡ የእግዚአብሐሔር መልአክ ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ሄደ፡፡ የደመናውም ዓምድ ከፊታቸው ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ቆመ፡፡ በግብጻውያን ሰፈርና በእስራኤል ሰፈር መካከል ገባ፤ በዚያም ደመናና ጨለማ ነበረ፡፡ በእስራኤል በኩል ግን ሌሊቱን አበራ፡፡ የግብጽ ሠራዊት የእስራኤልን ልጆች አልነኩም፡፡ ሙሴ በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ፡፡ እግዚአብሐሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው፡፡ ባሕሩንም አደረቀው ውኃውም ለሁለት ተከፈለ፡፡
የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ መካከል በየብስ ገቡ፤ ውኃው በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው፡፡ የግብጽ ሠራዊት ከነሰረገላዎቻቸው ከፈረሶቻቸውም ጋር ወደ ባሕሩ ገቡ፡ንጋትም በሆነ ጊዜ እግዚአብሐሔር በእሳትና በደመና ዓምድ ሆኖ የግብጽን ሠራዊት ተመለከተ፡፡ የሰረገሎቹንም መንኮራኩር ሰባበረ፡፡ ግብጻውያንም፡- "እግዚአብሐሔር ይዋጋላቸዋልና ከእስራኤል ፊት እንሽሽ" አሉ፡፡
እግዚአብሐሔር ሙሴን፡-"እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ ውኃውንም በግብጻውያን ሠራዊት ላይ ይመለስ" አለ፡፡ ሙሴም እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፤ ባሕሩም ወደ መፍሰሱ ተመለሰ፤ የፈርዖንም ሠራዊት ሰጠሙ፡፡ እስራኤላውያን የግብጻውያንን ሬሳ በባሕሩ ዳር ሆነው አዩ፡፡
እግዚአብሐሔር በኃይሉ ሕዝቡን ባሕር ከፍሎ አሻገረ፡፡ ነጻነታቸውን አቀዳጅቶ ከጠላት በትር አድኖ ወደ ዕረፍት መራቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሐሔር የሚሳነው (የማይችለው) ነገር የለም፡፡ ባሕርን ያለመርከብ ያሻግራል፤ በረሐውን እንደ ገነት አድርጎ ይመራል፡፡ በእሳት ውስጥ ሳይቃጠሉ ያኖራል፡፡ በእሳትና በውኃ መካከል በሕይወት ያሳልፋል፡፡

## አሠርቱ ቃላት

እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነጻ ወጥተው የበረሓውን ጉዞ ጀመሩ፡፡ በእግዚአብሔር ተራራ በሲና ግርጌ በሰፈሩ ጊዜ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ወደ ሲና ተራራ ወጣ፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ መናገር ጀመረ "ለያዕቆብ ቤት ለያዕቆብ ልጆች እንዲህ በል፤ በግብጻውያን ያደረግሁትን ከፈርዖን እጅ አውጥቼ ቀን በደመና ሽፍኜ ሌሊት ብርሃን አብርቼ ቀይ ባህርን ከፍዬ እንዳመጣኋችሁ አስተውላችኋል? አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጣችሁ ልጆችየ ርስት ትሆናላችሁ" አለው፡፡

ሙሴም ወደሕዝቡ መጣ፡፡ የሕዝቡን ሽማግሌዎች ጠርቶ እግዚአብሔር ያዘዘውን ይህን ቃል ሁሉ በፊታቸው ተናገረ፡፡ ሕዝቡ ሁሉ አንድ ላይ ሆነው "እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን፡፡" ብለው መለሱ፡፡ ሙሴም የሕዝቡን ቃል ወደ እግዚአብሔር አደረሰ፡፡ ሕዝቡም ልብሳቸውን አጠቡ ራሳቸውን አዘጋጁ፡፡

እግዚአብሔር ሕግጋቱን (ዐሥርቱን ቃላተ ኦሪት) ለሙሴ መንገር ጀመረ፡-

1. ግብጽ ምድር ከባርነትም ቤት ያወጣውህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።
2. የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፡፡
3. የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡
4. አባትና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም፡፡
5. አትግደል።
6. አታመንዝር።
7. አትስረቅ።
8. በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፡፡
9. የባልንጀራህ የሆነውን ሁሉ አትመኝ፡፡
10. ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ፡፡

ሙሴም ዐሥሩን ቃላት ተቀብሎ ወደ ሕዝቡ ተመለሰ፡፡ ሕዝቡም ሁሉ ነጎድጓዱንና መብረቁን የቀንደ መለከቱን ድምፅ ተራራውም ሲጨስ አዩ፡



፡እግዚአብሔር ሕገ ኦሪትን(ዐሥሩን ቃላት) ለሙሴ ሰጠ፡፡ ሙሴም ተቀብሎ ለሕዝቡ ነገረ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የመለየት ሥርዓትን የሚያጸና ሕግ ሰጥቷል፡፡ ልጆች እርሱን መውደዳችንን በሥራ ለመግለጽ በጸጋው እየተደገፍን ትእዛዛቱን እንድንፈጽም ይርዳን።